# <u>የራሷ እያረረባት የሰው ታማስላለች!</u>

ከአብነት (ዋሽንግተን ዲሲ)

በተመሰረተው AFD ህብረትና ራሱ ትብብሩ አወያይ በሆኑት ነጥቦች ዙርያ ደጋግመው መግለጫዎችን ሰጥተዋል። በስብሰባም ሆነ በረዲዮ ቃለ መጠይቆች እንደዚሁም በጽሁፍ አስረድተዋል። ይህም እኛው የሃገራችንን ጉዳይ በአንክሮ ለምንከታተለው ለማስረዳት ያደረጉት ጥረት መሆኑ የታወቀ ነው። ብዙዎች ኢትዮጵያውያንም ያላቸውን ስጋትና ተስፋ ሰንዝረዋል። አሁንም እንደቀጠሉበት ይገኛል። እኔም በህዝቡ ተሳትፎ በመበረታታት የግሌን እንድወረውር ወሰንኩ። ሶወስተኛው የአመሪካው ፕረዚዳንት ቶማስ ጀፈርሰን ዘላአለማዊና የማያቋርጥ ንቁ የህዝብ ተሳትፎ የዲሞክራሲ ዋጋ እንደሆነ መጠቆማቸውም ትዝ አለኝ። በመሆኑም የሚታየው ንቁ ተሳትፎ በበለጠ እንዲጎለብት እያሳሰብኩ ትብብሩን አስመልክቶ አንድ ሁለት እንድል ይፈቀድልኝ

"ለመስከረም 23/98 ሰልፍ የጠራው ህብረት፡ መስከረም 26/98 ዓ/ም ምክርቤት ስለመግባትና አለመግባት ጥያቄ ላይ ስብሰባ አካሂዶ 10 ለ3 በሆነ ድምፅ ህብረት ምክር ቤት መግባት የለበትም ብሎ ወሰነ። ላለመግባት የወሰነቱ አብዛኞቹ በውጭ ሃገሮች የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች ሲሆኑ መግባት አለብን ብለው የወሰኑት በሃገር ቤት በምርጫው ዋነኛ ተሳታፊ የነበሩት የእነ ዶ/ር ጴጥሮስና መራራ ጉዲና ድርጅቶች ሲሆኑ የኢትዮጵያ ህዝብ ሰልፍ እንዲወጣ ጥሪ ባሳለፉ በሳምንቱ በጉዳዩ ላይ እልባት ሳያበጁ ምክር ቤት ለመግባት ወሰኑ።" በመቀጠልም " የህብረት አባል ድርጅቶች ምክር ቤት ለመግባት በወሰኑበት ወቅት የህዝቡ ትግል በእንጥልጥል ላይ ይገኝ የነበረ ሲሆን ሃላፊነቱ ከመጀመርያውም ቢሆን ሰልፉን ባልጠራው በቅንጅት ላይ ወደቀ።" *(ግንቦት 7 ገጽ* 206 በክፍሉ ታደሰ)

ይህ እንግዲህ የህብረት የትናንት ታሪክ ነው። እላይ ታች ብሎ ደክሞና አምጦ የጠራው የህዝብ እምቢተኝነት ብቻ ነው የሚያዋጣው ብሎ ከዋሽንግተን ዲሲ የወሰነውን ዓብይ ጉዳይ ለህዝብ ካስተላለፈ በሃላ በዋናው ዕለት የመጀመሪያው እጅ ነሽ ሆኖ አረፈው። በእቅዱ ቀዳሚ ሆኖው ብዙም ባላሰቡበት ግን ተጠቂዎች ሆኖው እንዲቀሩ አደረገ። ይህ እንዳለ ሆኖ አሁን ሌሎች በፈጠሩት ትብብር ህብረት ላይና ታች ማለቱ ለምን አስፈለገ? የሞራል ብቃቱስ ከየት አመጣው? የራሱን መሪዎችን ብቃትና ችሎታ በመገምገም ሊያደርጉት የሚችሉትንና የማይችሉትን በቅጡ ያልለየው ህብረት አሁን ሌሎች በተለሙት የህብረት ጉዞ ደርሶ ለመተቸት መሞከር አሁንም አይናችሁ ጨፍኑና ላሞኛችሁ ካልሆነ ሌላ ትርጉም አይኖረውም።

ቅንጅቶች እኮ አንዴ ብቻ ነው ተቀናጅተው ወያኔን/ኢህአዴግን በማያዳግም የቀጡት። በመሆኑም ነው እስከ አሁን ድንጋጤው ሊለቀው ያልቻለው። ኢዴሃቅ፤ ፓሪስ አንድ፤ ፓሪስ ሁለት፤ ኢተፓድህና በመጨረሻም የሀው ያሁኑ ህበረት ያፈራብን ቢኖር ለራሳቸው የሚደክሙትን እንደነ ዶ/ር ጴጥሮስ በየነን ነው። የሚገርመው ከዚህ ሁሉ ስህተት ተምሮ እነኳ እንደመጸጸት፤ አሁንም የህብረት ኤክስፐርት እኔው ብቻ ነኝ ለማለት ይከጅላቸዋል። ወያኔዎች እኛ ያላፈረስነው ድርጅት የለም እንደሚሉት ሌላ የሰራውን ብቻ በመተቸት መኖሩና ጊዜ ማጥፋቱ ማንን ጠቀመ? ከምርጫው በፊትም ቢሆን ያራት/ስድስት ኪሎ ምሁራን ነን ባዮች ታማኝ ተቀዋማዊ ሆኖው

በማገልገል የኢህኣዴግን መንግስት ከማጠናከር ምን ሊያመጡ ነው በማለት የቅንጅት ሰዎችን ህብረት የሚባለው እንደተፈታተናቸው/እንዳብጠለጠላቸው የኢትዮጵያን ጉዳይ ለምንከታተል የሚዘነጋ ኣይደለም።

የራስህን ጉዳይ በትጋት ሰርቶ ለውጤት እንደመብቃት የሌላውን ስራ እግር በእግር እየተከተሉ ለማንኳሰስ መሞከር ካማንም በላይ ራስን ነው የሚያስገምተው። ለራሱ ለህብረቱ ካልሆነ በስተቀር ግልጽ ያልነበረው የሚያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃል ነውና የህብረት መሪዎች የኢትዮጵያን ህዝብ ኣሁን ላለበት ሁኔታ እንደሚዳርጉት ብዙም ኣሻሚ ኣልነበረም። ያስራ ኣምስት ድርጅቶች ስብስብ ነን፤ የሁሉም ብሄር/ብሄረ-ሰቦች በኣባልነት ኣሉበት የተባለለት ህብረት በምርጫው ወቅት በተደረገው ክርክር በሁለት ሰዎች ብቻ ይወከል ለመኖሩ ከላይ የጠቀስኩት ደራሲ በዚያው መጽሃፉ በገጽ 61 ያስረዳል። በሰሜን ኣመሪካም ሆነ በኣውሮፓ እንደዚሁ ሁለት ሁለት መሆናቸው ለማንም የሚታወቅ ጉዳይ ነው። ይህ ጉዳይ ማንሳት የፈለኩት ህብረት በተቋቋመው ትብብር ላለመግባት ከገደበው ምክንያት ኣንዱ በትብብሩ ውስጥ ካሉት ሌሎች ድርጅቶች የበለጠ ውክልና እንደጠየቀ ሊቀመንበሩ ኣቶ ዳውድ ኢብሳ በጁን 17 ለትንሳኤ ሬድዮ በሰጡት ቃለ-መጠይቅ በማብራራታቸው ነው። ሃቁ ይህ ሳለ ህብረት በመደጋገም ይፋ ሲያደርገው የቆየ ምክንያት ግን በትብብሩ "ኢትዮጵያ" የሚል ስም ኣለመታከሉ ነው። ጊዜ የሰጠው ቅል ድንጋይ ይሰብራል ሆኖ እነሆ የኢትዮጵያን ኣንድነት ኣስመልክቶ ቅንጅቶች በታንድ፤ በኢህኣፓና በመኤሶን መሪዎች ጥያቄ ውስጥ እንዲገቡ ሲሞከር ለማየት በቃን።

በምርጫው ኣከባቢ ወቅት ለብሄሮችና ብሄረ-ሰብ ጥያቄዎች ደንታ የሌለው ኣስመስሎ ለማቅረብና ለማሳጣት እንዳልተሞከረ ሁሉ፤ ኣሁን ደግሞ ከትልቁና ኣናሳዎቹ ባንድ ቃል ተጨቆን ከሚሉት ቅንጅት ትብብር መፍጠሩ ሌላ ችግር ሆነበት ለህብረት። እዚህ ላይ የተከበሩ ኣምባሳደር ዘውዴ ረታ ስለ ኣቶ ወልደ-ኣብ ወ/ማርያም ያሰፈሩትን ትውስታ በማጋራት ኣስተያየቴን ባጠቃልል ጠቃሚ ሳይሆን ኣይቀርም። ኣስፋሃ ወ/ሚካኤል በኤርትራ የንጉሰ-ነገስቱ እንደራሴ ስለ ኣቶ ወ/ኣብ ወልደማርያም በማስታወቅያ ሚኒስተር የም/ሚኒስተር ቦታ ቢሰጣቸው ስለሚኖረው ጥቅም ለቀ/ሃይለስላሴ በዘረዘሩት ጉዳይ ላይ የጠ/ሚ ኣክሊሉ ኣስተያየት እንደሚከተለው ሰፍረዋል። "ወልደኣብ ወልደማርያም በተፈጥሮው እምቢተኛ የሆነ ሰው ነው። እንደዚህ የመሳሰሉት ሰዎች ህይወታቸውን ሙሉ ማንኛውንም ነገር ሲቃወሙ የሚኖሩ ከመሆናቸውም የተነሳ ኣንዳንድ ጊዜ ከመሰረቱ ሲጥሩበት ከነበረው የራሳቸው ከሆነውም ሃሳብ ጋር ሲጣሉ ይገኛሉ። እኔ ወልደኣብን የማየው በዚህ መልክ ነው።" *(የኤርትራ ጉዳይ ገጽ 386)*